# የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት
# (በከተማ)

## የመጠይቅ እርማት (ኢዲቲንግ) እና ኮድ አሰጣጥ
## አጠቃላይ መመሪያ

## I. መግቢያ

ወቅታዊና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች መኖር የአንድን አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ፣ ዕቅድ ለማውጣት፣ ተግባራዊነቱንም ለመቆጣጠርና እያንዳንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ለሀገር ሀብት ውጤት ያለውን ድርሻ ለመከታተል አስፈላጊነቱ እሙን ነው፡፡

ከላይ የቀረበውን አጠቃላይ ዓላማ መሠረት በማድረግ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፍ ጥናቶች አማካኝነት ስታቲስቲካዊ መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ለተጠቃሚዎች የጥናቱን ውጤት ሲያሠራጭ የቆየና አሁንም የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም መሠረት በትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች በኩል ያለውን የፋብሪካዎች ብዛት፣ በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት፣ የምርት መጠንና ዓይነት፣ የሚጠቀሙባቸው የጥሬ ዕቃዎች ዓይነትና መጠን፣ የሚጠቀሙባቸው የቋሚ ንብረቶች ዓይነትና መጠን የመዋዕለ ንዋይ መጠን ...ወዘተ የሚመለከቱ አስተማማኝ መረጃዎች ለማስገኘት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት በየዓመቱ ያከናውናል፡፡

የዚህ ጥናት መረጃ ከመስክ ተሰብስቦና ውጤቱ ተጠናቅሮ ለተጠቃሚዎች እስከሚሠራጭ ድረስ ብዙ የጥራት መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ያልፋል፡፡ በተለይም ኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ የተሰበሰቡ መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድ አድርጎ ለመረጃ ማቀናበር የማስተላለፍ ሥራ እንደመሆኑ መጠን እርማት የማድረጉ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይገባዋል፡፡ በዚሁ ሥራ ላይ የሚሣተፉ ሠራተኞች አንድ ዓይነት የአሠራር (የአስተራረም) ዘይቤ እንዲከተሉ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## II. <u>ትርጉም</u>

1. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ የሚባለው በአማካይ አሥርና በላይ በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ያሉበትና በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፣ አብኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርት ፋብሪካ ሁሉ የሚያካትት ነው፡፡

   ለምሣሌ፣ የዳቦ መጋገሪያ፣ ምግብ ዘይት ማምረት፣ የልብስ ስፌት፣ የሹራብ ሥራ፣ የሕትመት አገልግሎት፣ የእንጨት መሰንጠቂያ፣ የብሎኬቶች፣ የቱቦዎች፣ የግድግዳና የወለል ሽክላዎችና የወለል ጡቦች፣ የወርቅ ማንጠር፣ የቤትና የቢሮ ዕቃዎችና የመሳሰሉትን ማምረትን ያጠቃልላል፡፡

<u>ማምረት (ማምረቻ)</u>፣ ተብሎ የተጠቀሰው የጥሬ ዕቃዎችን፣ ወይም የመገጣጠሚያዎችን ቅርጽ ወይም/ እና ይዘት መካኒካዊ ወይም ኬሚካላዊ የሆነ ዘዴ በመጠቀም ወደ አዲስ ውጤት የመለወጥና የአካል መገጣጠም ሥራዎችን የማከናወን ተግባር ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ምርቱ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል በመጠቀም የሚከናወን እስከሆነ ድረስ በጅምላ ወይም በችርቻሮ የተሸጠ/የሚሸጥ ሊሆን ይችላል፡፡

2. ኢዲቲንግ፡- ማለት ለዚህ ጥናት ከየፋብሪካዎች ተሰብስቦ የመጣውን መረጃ በተሰጠው የእርማት ዘዴዎች መሠረት በማስተካከል፣ ከመመሪያው ውጭ የተሠራ ከአለ በመመሪያው መሠረት በማረም የሚቃረኑ መረጃዎች ከተሞሉ ተስማሚ እንዲሆን በማድረግና ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎችን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከሌሎች ዓምዶች ጋር በማስተያየትና የሂሣብ ሪፖርት ከአለ በማገናዘብ እንዲሞሉ በማድረግ የተሞሉ መጠይቆችን ጥራት የማሻሻል ሥራ ነው፡፡

3. ኮዲንግ፡- ማለት መጠይቁ ላይ በቃላት የተሰጡትን መልሶች ወደ አሃዝ በመለወጥ ወደ ኮምፒዩተር መረጃውን ለማስገባትና መረጃውን ለማቀነባበር የሚረዳ ተግባር ነው፡፡

## III. ጠቅላላ መመሪያ

በትክክል የተሞላ መጠይቅ ከሚኖሩት ባህርያት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ለጥያቄዎቹ የተሰጡት መልሶች በሙሉ ግልጽና ለኢንኮደሮች በሚታይ ሁኔታ የተሞላ መሆን አለበት፡፡

2. ሁሉም መልሶች በመጠይቅ አሞላል መመሪያና በኢዲቲንግ መመሪያው መሠረት የተሞሉ መሆን አለባቸው፡፡

3. በመልሶቹ መካከል ቅራኔ መኖር የለበትም፡፡ ይህም ማለት አንድ ቦታ የተሰጠው መልስ ሌላ ቦታ (ጥያቄ ላይ) ከሚሰጠው መልስ ጋር መቃረን የለበትም፡፡ በኢዲቲንግ ጊዜ እነዚህንና ሌሎች ተመሳሳይ ባህርያት ተሞልቶ በመጣው መጠይቅ ላይ መኖራቸውን በማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርማቶችን ማድረግ (እርማት ሊደረግባቸው በሚገባ ቦታዎች ብቻ) ያስፈልጋል፡፡

የኢዲተሩ እርማት ከጠቅላላው መረጃ ጋር መስማማት አለበት፡፡ ምክንያቱም የዚህ መረጃ ብቸኛ ምንጭ በመጠይቁ ላይ የተሞላው መረጃና የሒሣብ ሪፖርት ከተያያዘ የሒሣብ ሪፖርቱ ነው፡፡ ማንኛውም ኤዲተሩ በዚህ መመሪያ መሠረት ሊያቃልለው ያልቻለው ጥያቄ በሚያጋጥመው ወቅት ወይም በመመሪያው ውስጥ ያልተካተቱ የአሠራር (የአስተራረም) ችግሮች ሲያጋጥሙት ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው የተቆጣጣሪ (ባለሙያ) በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ አለበት፡፡ ኢዲተሩ መልስ ላልተሞላላቸው ጥያቄዎች በምንም ዓይነት የሚመስለውን መልስ ፈጥሮ መጻፍ ወይም እርማት በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ባለሙያ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢው ያሠፈረውን መልስ መፋቅ/ማጥፋት የለበትም፡፡

ከላይ በቀረበው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የተሞሉ መጠይቆች እርማት ሥራ በሚከናወንበት ወቅት የሚከተሉትን የኢዲቲንግ የአሠራር ስልቶች በመከተል የተሞላውን መጠይቅ እንደገና መመርመር ያስፈልጋል፡፡

## 1. ኮድ ማድረግን በሚመለከት፣

በዚህ መጠይቅ የተሞሉት መረጃዎች አብዛኛዎቹ አስቀድመው ኮድ ተደርገዋል:: በጣም የተወሰኑ የመጠይቁ ክፍሎች ለምሣሌ የአካባቢ መለያ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ክፍተኛ፣ የፋብሪካው መደብ፣ የፋብሪካው ተራ ቁጥር ...ወዘተ እና የምርት፣ የጥሬ ዕቃ፣ የመለኪያና የመሳሰሉት በቅድሚያ ኮድ ያልተደረጉት በኢዲቲንግ ሥራ ወቅት ኮድ መደረግ ይኖርባቸዋል:: ኮድ የተደረጉትም ቢሆን በሚሰጠው የኮድ ዝርዝር መሠረት እንደገና ትክክለኛነታቸው መጣራት ይኖርበታል:: መረጃው የሚቀነባበረው በኮምፒዩትር እንደመሆኑ መጠን የጥናቱ ትንተና የሚሠራው ለጥያቄዎቹ በተሰጠው ኮድ አማካይነት ብቻ ስለሆነ በዚህ በኩል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::

## 2. ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎችን ማረም፣

ሥራውን ለማከናወን መነሻው ከየፋብሪካው የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ በትክክል ተሞልቶ መምጣቱንና የመጠይቁ ገጾች ሙሉ መሆናቸውን አረጋግጦ መረከብ ያስፈልጋል:: መጠይቁ የሚሞላለት ፋብሪካ የማይመለከተው ክፍሎች ካሉ መረጃ ሰብሣቢው ክፍሉን በሚመለከት ጥያቄ ማቅረቡን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ሠረዝ በማድረግ ማለፍ እንዳለበት በመጠይቅ አሞላል መመሪያው ላይ የተገለጸ ቢሆንም በተግባር ላይከናወን ስለሚችል እንደገና ማየት ተገቢ ይሆናል:: የተሰጠውን የእርማት መመሪያ በመከተል በመጠይቁ ላይ ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎችን በሚመለከት አስፈላጊው እርማት ይደረጋል:: ሳይሞሉ በቀሩ መረጃዎች ፋንታ የሚሞላው መረጃ የሚገኘው በሌሎች ክፍሎች የተሞሉ መረጃዎችን በማገናዘብና በመመርመር እንዲሁም ፋብሪካው የሂሣብ መዝገብ ከአያያዘ የሂሣብ መዝገቡን በመጠቀም ነው:: ሆኖም ሳይሞሉ ለቀሩት መረጃዎች በመጠይቁ ከታዩት መረጃዎች ጋር አመሳክሮና መርምሮ ወይም የሂሣብ መዝገብ ላላቸው ከሂሣብ መዝገቡ ጋር ተያይቶ ሊታረም የማይችል ከሆነ ፈጥሮ መሙላት የማይቻል ስለሆነ ለሚመለከተው ክፍል ሁኔታውን ማቅረብ ያስፈልጋል::

## 3. *የማይመሳሰሉና ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችን ማረም፣*

የማይመሳሰሉና ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችን በእርማት ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል:: ሊሆነ የማይችሉ መልሶች ሲባል በመጠይቅ አሞላል መመሪያው ከተሰጠው ውጪ የተመለሱ ማለት ነው:: ለምሣሌ፣ በመመሪያው መሠረት የፋብሪካው የሂሣብ መዝገብ ሁኔታ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ሊሆን የሚችለው የተሞላ ኮድ «1» ወይም ገቢና ወጪ ኮድ «2» ወይም ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ የለውም ኮድ «3» ብቻ ነው:: ሆኖም የተሰጠው መልስ ከዚህ ውጭ ኮድ «4» ወይም ኮድ «5» ቢሆን የማይመሳሰል ወይም ሊሆን የማይችል መልስ ስለሆነ ከሚቀጥለው ጥያቄ ጋር በማገናዘብ መታረም አለበት::

## 4. *የሚቃረኑ መልሶችን ስለማረም፣*

የሚቃረኑ (እርስ በርሳቸው የሚጋጩ) መልሶችን ማረም ተገቢ ነው:: የሚቃረኑ መልሶች የሚገኙት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሊዛመዱ የሚችሉ መልሶች ሳይዛመዱ ሲቀሩ ነው:: ለምሣሌ፣ በክፍል 4.2 ዓምድ 4 ላይ በተገዙበት ሁኔታ ለተሸጡ ዕቃዎች የተደረገ ገቢ አለ ተብሎ ከተመዘገበ፣ በክፍል 6.2 ዓምድ 12 ላይ በተገዙበት ሁኔታ ተመልሰው ለተሸጡ ዕቃዎች የተደረገ ወጪ ቢያንስም ቢበዛም ተሞልቶ መገኘት አለበት:: ነገር ግን አንደኛው ተሞልቶ ሌላኛው ሳይሞላ ቢገኝ ሁለት መዛመድ የሚገባቸው መልሶች ስላልተዛመዱ እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት የተሞላውን መልስ ከሌላኛው ጋር ማገናዘብና ማስተካከል ወይም ሁኔታውን ለሚመለከተው ክፍል (ከፋብሪካው) በመጠየቅ ማስተካከል ያስፈልጋል::

## 5. *መረጃ ሰብሣቢው ከአስተያየት ጋር መልስ የሰጠባቸውን መልሶች በሚመለከት፣*

እንደነዚህ ዓይነት መልሶች በእርማት ወቅት ልዩ ጥንቃቄ የሚሹ ስለሚሆን ከመታረሙ በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: የሂሣብ ሪፖርት ከአለ በማገናዘብ ለማስተካከል ይቻላል፤ ይህ ካልሆነ ግን የሚመለከተውን ክፍል (ፋብሪካውን) በማነጋገር መፍትሔ መፈለግ ተገቢ ነው::

## 6. በየዓምዶቹ የቁጥሮችን አጻጻፍ በሚመለከት፣

በእያንዳንዱ ዓምድ ሥር ባሉት ካርድ ኮለሞች /ንዑስ ዓምዶች/ ውስጥ የተሞላውን የቁጥሩን መጨረሻ በስተቀኝ ባለው የመጨረሻ ቦታ (ካርድ ኮለም) በመጀመር የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## 7. የመጠን መለኪያን በሚመለከት፣

በዚህ መጠይቅ ውስጥ መጠንን በሚመለከት መሞላት ያለበት የሜትሪክ መለኪያን በመጠቀም መሆን ይገባዋል፡፡ መረጃ ሰብሣቢው ከሜትሪክ መለኪያ ውጪ ሞልቶ ከተገኘ ከሚሰጠው የኮድና የመለኪያ ዝርዝር ጋር በማገናዘብ እንደገና ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡

## 8. አማራጭ መልሶች ያላቸውን ጥያቄዎች በሚመለከት፣

በእያንዳንዱ ጥያቄ ሥር በተተወው ባዶ ቦታ ላይ በተጻፈው ወይም በተከበበው ቁጥርና በኮድ መስጫው ሣጥኖች ውስጥ የተሞላው ቁጥር አንድ ዓይነት መሆኑን በሚገባ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ አነጋገር የዚህን መጠይቅ የኢዲቲንግ ሥራ በሚገባ ለማከናወን ኤዲተሩ ከላይ የቀረቡትን የአስተራረም ዘዴዎች ብቻ ሣይሆን ስለመጠይቁም ከመረጃ ሰብሣቢው በበለጠ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የትኛው መልስ (ዓምድ) ከየትኛው መልስ (ዓምድ) ጋር መገናዘብ እንዳለበት መረዳት ስላለበት ነው፡፡ ስለሆነም በኢዲቲንግ ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ወይም የመጠይቁን የተለያዩ ክፍሎች/ዓምዶች እርስ በርሱ በማይጋጭ መንገድ ተገናዝቦ በሚገባ የተሞላ መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ከላይ ከቀረቡት አጠቃላይ ማስገንዘቢያዎች በተጨማሪ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ዓምድ በዓምድ የቀረቡትን የማስተካከያ ዘዴዎች በመከተል ኤዲተሩ የተሞላውን መጠይቅ መመርመር አለበት፡፡

# የ1996 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ዝርዝር የኢዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ

## ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ፣

ከዓምድ 1-13 ፋብሪካው የሚገኝበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ ክፍለ ከተማ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር፣ የስልክ ቁጥርና የፖ.ሣ.ቁ. ከተሰጣቸው ኮድ ጋር ተገናዝበውና አንዳቸውም ሳይዘለሉ በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከእነዚህ ዓምዶች አንዱ ሳይሞላ ቢቀር በሌሎች ዓምዶች ውስጥ ከተመዘገቡት መረጃዎች በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል። ለምሣሌ፣ ከአዲስ አበባ ውጪ ላሉት በዓምድ 1 ውስጥ የክልል ስምና በዓምድ 3 ውስጥ የወረዳ ስም ተመዝግቦ በዓምድ 2 ውስጥ የዞን ስም ሳይሞላ ቢቀር የክልሉንና የወረዳውን ስም በማየትና በማገናዘብ የዞኑን ስም ለይቶ መጻፍ ይቻላል። በተጨማሪም ቀደም ላሉ ዓመታት ለድርጅቱ ከተሞሉ መጠይቆች በማገናዘብ መሙላት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ በተራ ቁጥር 1.1 እና 1.2 ከክልል የቤት ቁጥር (ከዓምድ 1-7) በተሰጠው የአካባቢ መለያ ኮድ መሠረት በየዓምዶቹ ሥር በሚገኙ ካርድ ኮለሞች ውስጥ በትክክል ኮዳቸውን መመዝገብ ያስፈልጋል።

<u>ተራ ቁጥር 1.1 - ዓምድ 9 - የፋብሪካው መደብ፣ በጥያቄ 2.1 ሥር በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ፋብሪካው የሚያመርተው ምርት መጻፉን ማረጋገጥና (በ2.1 ላይ ካልተጻፈ ከ4.1 ዓምድ 2 ላይ ወስዶ በመጻፍ) የዓምድ 9 የኮድ መስጫ ባታው በመረጃ ሰብሣቢዎች የማይሞላ ስለሆነ ለዚህ ከተዘጋጀው የኮድ መመሪያ</u> "ISIC" (የኢንዱስትሪ ዓይነት መለያና ኮድ ዝርዝር) ላይ በመውሰድና ተስማሚውን ባለ አራት ዲጂት ኮድ በመምረጥ በጥንቃቄ መሞላት ይኖርበታል። ከአንድ በላይ በነጠላ ሠረዝ የተጻፈ ምርት ካጋጠመ በመጀመሪያው (በዋናው ምርት በሚያስገኘው ገቢ መሠረት) ኮዱ ይሞላለታል። ሆኖም የድርጅቱ የምርት ዓይነት ቀደም ሲል ወይም በ1995 ዓ.ም ከነበረው የተለየ ከሆነ ከሚመለከተው ባለሙያ ጋር በመነጋገር ኮድ መስጠት ያስፈልጋል።

ተራ ቁጥር 1.1 - ዓምድ 10 - የፋብሪካው ስምና ተራ ቁጥር፣ በዚህ ዓምድ የፋብሪካው ስም ወይም ፋብሪካው ስም ከሌለው የባለቤቱ/የባለቤቶቹ ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ መጻፉንና በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ የመለያ ቁጥር (የፋብሪካው ተራ ቁ.) ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ስሙ ካልተሞላ ግን ከመጠይቁ ሽፋን ወይም ጀርባ ላይ በመውሰድ መሞላት አለበት:: የፋብሪካው ተራ ቁጥር የሚሞላው በጥናቱ የተሸፈኑ ፋብሪካዎች በሙሉ የኢንዱስትሪ ዓይነት ምደባ ኮድ በዓምድ 9 ከተሰጣቸው በኋላ በመጨረሻ ላይ ይሆናል:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ የሚሞላው ተራ ቁጥር (ኮድ) የኤዲቲንግና ሌላው የኮዲንግ ሥራ ካለቀ በኋላ በሚሰጠው መመሪያና ዝርዝር መሠረት የሚፈጸም ይሆናል::

ተራ ቁጥር 1.1 - ከዓምድ 12-13 እና ተራ ቁጥ 1.2 ከዓምድ 8-9፣ በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ የፋብሪካው ስልክና የፖ.ሣ.ቁ. መሞላቱን ከሌለ ደግሞ ሠረዝ መደረጉን ማየት ያስፈልጋል::

## <u>ክፍል 2 - ስለ ፋብሪካው መሠረታዊ መረጃዎች፣</u>

**2.1** <u>ፋብሪካው የሚያመርተው ምርት፣</u> በክፍል 1.1 ዓምድ 9 የፋብሪካውን መደብ በዚህ መረጃ መሠረት መሙላት እንዳለብንና ካልተሞላ በ4.1 ዓምድ 2 መሠረት ማስተካከል እንደሚገባ የተገለጸ ስለሆነ በዚያው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል::

**2.2** <u>ፋብሪካው ቅርንጫፎች ካሉት ብዛታቸው ስንት ነው</u>? መረጃው ከሚሞላለት ፋብሪካ ውጪ ያሉት የቅርንጫፍ ፋብሪካዎች ብዛት በአሞላል መመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

**2.3** <u>ፋብሪካው ሥራ የጀመረበት ወርና ዓመተ ምሕረት መቼ ነው</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር በተዘጋጀው ካርድ ኮለም ፋብሪካው ሥራውን የጀመረበት ወርና ዓመተ ምሕረት በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የግድ መሞላት ይኖርበታል:: ስለዚህ በተሰጠው ቦታ ላይ በመጀመሪያ ወሩ ቀጥሎ ዓመተ ምሕረቱ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሣጥኖች (ካርድ ኮለሞች) ከ01-12 ብቻና በሚቀጥለው አራት ኮለሞች ሥር እስከ 1996 ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: በአውሮፓውያን አቆጣጠር ለተሞሉ ስባት/ስምንት ዓመት በመቀነስ መሙላት ያስፈልጋል::

2.4 <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪው የሂሳብ መዝገብ ሁኔታ</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር ከተሰጡት ሦስት አማራጮች አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡን ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ሂሳብ መዝገብ ካለው ከዚያ ጋር በማመሳከር ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

2.5 <u>ፋብሪካው የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ከሆነ በየትኛው ዘመን አቆጣጠር ነው</u>?
በዚህ ጥያቄ ሥር ከ1-4 ከተሰጡት አማራጭ ኮዶች ውስጥ አንዱ ኮድ ብቻ የተከበበና ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱንና የተከበበው 4ኛው ተራ ቁጥር ከሆነ ዘመኑ መገለጽ እንዳለበት ማረጋገጥ ይኖርብናል:: በተጨማሪም በጥያቄ 2.4 ላይ ኮድ «2» የተሞላላቸው ፋብሪካዎች ይህ ጥያቄ ስለማይመለከታቸው በስህተት ከተሞላ ማስተካከል ያስፈልጋል::

2.6 <u>የፋብሪካው የባለቤትነት ይዞታ ምንድን ነው</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር ከተሰጡት ሶስት አማራጮች አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡን ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ኮድ 3 ለተሞላላቸው ድርሻ በመቶኛ መሞላቱን ማየት ተገቢ ነው::

2.7 <u>የማምረቻው ኢንዱስትሪው ከመንግሥት ወደ ግል የተዘዋወረ ነውን</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር ከተሰጡት ሁለት አማራጮች አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡንና ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ይህ ጥያቄ የሚመለከተው ለጥያቄ 2.6 ኮድ 1 ወይም 3 ለተሞላላቸው ብቻ የሚጠየቅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

2.8 <u>ከመንግሥት ወደ ግል የተዘዋወረበት ወርና ዓመተ ምህረት፣</u> በዚህ ጥያቄ ሥር በተዘጋጀው ካርድ ኮለም ፋብሪካው ወደ ግል የተዘዋወረበት ወርና ዓመተ ምህረት ለጥያቄ 2.7 መልስ ኮድ 1 ለመለሱ ሁሉ የግድ መሞላት አለበት::

2.9 <u>በተራ ዙጥር 2.6 ኮድ 1 እና 3 (የግሉ ድርሻ 51 ፐርሰንትና በላይ) ለተሞላላቸው የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም ምንድን ነው</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር ከተሰጡት ከ1-7 አማራጮች አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡንና ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

**2.10** <u>በ2.7 የባለቤትነት ዓይነት ለተሞላላቸው የፋብሪካው ባለቤቶች ብዛት በየታ ይገለጽ</u፣ በግል/በሕብረት ሥራ ማህበር፣ በመንግሥትና በግል (የግሉ ድርሻ 51 ፐርሰንትና በላይ) ለተያዙ ፋብሪካዎች ብቻ የፋብሪካው ባለቤቶች ብዛት በየታ በዓምድ 7 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በ2.7 የተሞላው ኮድ 1 መሆን (በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት የሚመራ) የፋብሪካው ባለቤቶች ብዛት ከአንድ መብለጥ የሌለበት ሲሆን መሞላት ያለበት ወንድ ወይም ሴት በሚለው እንጂ በሁለቱም አለመሆኑ መረጋገጥ ይገባዋል:: በመጨረሻም በድምሩ ቦታ የተሞላውን እንደገና በመድመር ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

**2.11** <u>የማምረቻው ኢንዱስትሪው የማምረቻ ሥራውነ ለመጀመር ምን ያህል ገንዘብ አወጣ?</u> ይህ ጥያቄ የማምረቻ ኢንዱስትሪው ሥራውን ለመጀመር የድርጅቱ ባለቤቶች ያዋጡት/የከፈሉት የገንዘብ መጠን የድርጅቱን ሥራ ለመጀመር ቋሚ ንብረቶችን ለመግዛት/ለመከራየት ያዋጡትንን ለሥራ ማስኬጃ የከፈሉትን የገንዘብ መጠን በሙሉ የሚያካትት መሆን ይገባዋል:: በዚህ መሠረት ኢትዮጵያዊያንን በጾታ በመለየት ኢትዮጵያዊ ካልሆኑ በጾታ ሳይለይ የተዋጣውን የገንዘብ መጠን በብር በየአንፃራቸው በተሰጡት ክፍት ቦታ መሞላቱንና ከነኑ ባሉት ካርድ ኮለሞች ውስጥ የገንዘቡ መጠን ተደግሞ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ከአንድ እስከ 5 ባሉት ክፍት ቦታዎች የተሞሉት ድምራቸው በስድስተኛው ክፍት ቦታ ከተሞላው እኩል መሆኑን ማረጋገጥ የስፈልጋል::

**2.12** <u>ፋብሪካው በጥናት ዓመቱ መጨረሻ የደረሰበት ካፒታል</u>፣ ፋብሪካው በጥናት ዓመቱ መጨረሻ የደረሰበት ካፒታል ኢትዮጵያዊ ካልሆኑ በጾታ ሳይለይ የተሞላ ሲሆን ይኸውም የደረሱበት የካፒታል መጠን በየአንጻራቸው በተሰጠው ካርድ ኮለሞች መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪ ከ1-5 በተሰጡት ክፍት ቦታዎች የተሞሉትን ቁጥሮች ከድምሩ ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፧

**2.13** <u>ፋብሪካው በ1996 ዓ.ም ለምን ያህል ወራት ሠራ በሙሉ ወር ይገለጽ፣</u>
በዚህ ጥያቄ አቅጣጫ በተሰጠው የኮድ መስጫ ሣጥን ውስጥ በ1996 ዓ.ም ፋብሪካው ለምን ያህል ወራት እንደ ሠራ ከ1-12 ወራት ብቻ መገለጽ ይኖርባቸዋል:: ፋብሪካው ከ15 ቀናት በታች በዓመቱ ከሠራ በጥናቱ ስለማይካተት «00» የሚል ቁጥር ሊኖር ወይም ከ12 ወራት በላይ ቁጥር ሊሞላ

ስለማይችል ከዚህ ውጭ ከተገኘ ከሚቀጥለው ጥያቄ ጋር በማስተያየት መስተካከል ይኖርበታል፡፡

**2.14** ፋብሪካው ሙሉውን ዓመት ካልሠራ ያልሠራባቸው ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች በቅደም ተከተላቸው ይገለጽ፡፡ በዚህ ጥያቄ ሥር ከ1-10 ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ሶስት ኮዶች ብቻ መከበባቸውንና እነዚህ የተከበቡ ኮዶች በኮድ መስጫው ሣጥኖች (ካርድ ኮለሞች) ውስጥ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያለብን ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ መልሱ ከሶስት ሊበልጥ ባይችልም ከሶስት ያነሰ መልስ ግን ሊሞላ ስለሚችል ማስተካከሉ በዚሁ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

**2.15** የፋብሪካው የማምረቻ ሕንፃ (ቤት) ይዞታ፣ በዚህ ጥያቄ ሥር ከተሰጡት ከ1-3 አማራጮች አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡን ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**2.16** ለጥያቄ 2.12 መልሱ የግል ወይም ኮድ 1 ከሆነ ምንጩ ምንድነው? በዚህ ጥያቄ ሥር ከተሰጡት አማራጭ ኮዶች ውስጥ አንዱ ኮድ ብቻ የተከበበና ይኸው ኮድ በኮድ መስጫው ሣጥን (ካርድ ኮለም) ውስጥ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## ክፍል 3 - በ1996 ዓ.ም በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ (በብር)፣

**3.1** በ1994 ዓ.ም በአማካይ በፋብሪካው ሥራ ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት፣

ከዓምድ 1-2፣ እነዚህ ዓምዶች አስቀድመው የተሞሉ ስለሆነ ምንም አይሞላም፡፡

ከዓምድ 3-14፣ በእነዚህ ዓምዶች ውስጥ በየሙያ መደቡ በተጠቀሱት ወራቶች ውስጥ የሠራተኞች ብዛት በፆታ መሞላቱን ወይም የማይመለከታቸው ክፍሎች ሠረዝ መደረጋቸውን በመጀመሪያ ማየት ይኖርብናል፡፡ ከዚያም በፆታ በተጠቀሱት አራት ወራት ተለይቶ የተሞላው የሠራተኞች ቁጥር ከድምሩ (ቁልቁል) ጋር ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለምሣሌ በዓምድ 2 በተሰጠው የሙያ መደብ መሠረት በዓምድ 3 በመስከረም ወር የተሞላው የወንዶች ሠራተኞች

ብዛት በዓምድ 3 በተራ ቁጥር 7 አቅጣጫ የተሞላውን ድምር መስጠት ይገባዋል፡፡

ዓምድ 15፣ በዚህ ዓምድ ላይ የተሞላው ሰዎች/በወራት በቀጥታ በጥናቱ ወቅት የነበሩ ጊዚያዊ ሠራተኞች ቁጥር አለመሆኑን (የነበሩ ጊዜያዊ ሠራተኞች ቁጥር ሲባዛ በሠሩት ወራት መሆኑን) ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን በበለጠ ለማረጋገጥ በዚሁ ክፍል ዓምድ 16 ላይ የተሞላውን የምንዳ መጠን በዓምድ 15 ላይ በተራ ቁጥር 6 አቅጣጫ ሰዎች/በወራት አካፍለን (የምናገኘው የአንድ ጊዜያዊ ሠራተኛ ወርሃዊ ደመወዝ ከ50-500 ብር አካባቢ በላይ ወይም በታች አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡

## 3.2 <u>በ1996 ዓ.ም የተከፈለ ደመወዝ፣ ምንዳ እንዲሁም ሌሎች የሠራተኞች ጥቅሞች (በብር)፣</u>

<u>ከዓምድ 3-6 ቅንስናሽ ሳይደረግ የተከፈለ የዓመቱ ደመወዝና ምንዳ፣</u>

በክፍል 3.1 ላይ ካሉት አራት ወራት በየትኛውም ወር በሁለቱም ፆታ የሰው ኃይል ቁጥር ከተሞላ በዚህ ክፍል ከዓምድ 3-4 ላይ ደመወዝ በሁለቱም ፆታ መሞላት ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ የውጭ ዜጋ ሠራተኞች ከአሉ ደመወዝ ላይም መታየት ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዱ ፆታ ብቻ ወይም የውጭ ዜጋ በሚለው ብቻ የሰው ኃይል ቁጥር ከታዬ ደመወዙም በተመሳሳይ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዓመቱ ቅንስናሽ ሳይደረግ የተከፈለው ጠቅላላ ደመወዝ በአማካይ ከነበረው የሰው ኃይል ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ለማወቅ የዓመቱን ደመወዝ ለነበረው አማካይ የሰው ኃይል አካፍሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በፆታ ለያይቶ በማካፈል ጭምር ማየት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚገኙት ውጤቶች የትርፍ ጊዜ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት ሊታሰብ ከሚችለው በላይ (ለምሣሌ ከ100 ብር በታች ወይም ከ1500 ብር በላይ) አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ፋብሪካዎች የጊዜያዊ ሠራተኞች ደመወዝን በክፍል 3.2 ደግመው ሊያስመዘግቡ ስለሚችሉ ይህ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ ክፍል ዓምድ 9 ፋብሪካው ለሠራተኞች ለጡረታና ለሕይወት ኢንሹራንስ የከፈለው የመንግሥት ፋብሪካ ከሆነ የጠቅላላ ደመወዝን 6 መቶኛ መብለጥ

አለበት (የትርፍ ጊዜ ክፍያና የሕይወት ኢንሹራንስ ግምት ውስጥ ስለሚገባ)። በመጨረሻም ቁልቁልና ወደ ጎን የድምሩን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ይኖርብናል።

3.3 <u>የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሚያገኙት መደበኛ ደመወዝ አመዳደብ</u>፣
የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሚያገኙት ደመወዝ አመዳደብ መሠረት ከዓምድ 3-15 ያለው ድምር ዓምድ «16»ን መስጠቱንና በፆታ ተለይቶ በሰኔ ወር ላይ በክፍል 3.1 በተራ ቁጥር 3 እና 4 አቅጣጫ ዓምድ 12፣ 13 እና 14 ላይ ያሉት ሲደመሩ ከሚገኘው የቅጥር ሠራተኞች ጋር፣ እንዲሁም ዓምድ 16 ቁልቁል ሲደመር ከዓምድ 12-14 በተራ ቁጥር 3.4 ከተሞላው የሰኔ ወር ቅጥር ሠራተኞች ድምር ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

# <u>ክፍል 4 - በ1996 ዓ.ም ፋብሪካው ያመረታቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ (በብር)</u>

4.1 <u>በ1996 ዓ.ም የፋብሪካው ዓመታዊ ምርትና ሽያጭ</u>፣

<u>ዓምድ 3 መስፈሪያ</u>፣ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ፋብሪካው ለሚያመርታቸው ዋና ዋና ምርቶች በዚህ ዓምድ መስፈሪያቸው በሜትሪክ መለኪያ መሰጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ከሜትሪክ መለኪያ ውጭ ለተሞላላቸው ከፋብሪካው ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመነጋገር ማስተካከያ መደረግ ይኖርበታል።

<u>ዓምድ 4 - የምርት ኮድ</u>፣ ይህ ኮድ የሚሞላው በምርት ኮድ መመሪያው ላይ ኮድ ለተሰጣቸው ምርቶች ብቻ ነው። ለሌሎች ምርቶች ዓምዱ በሠረዝ ይታለፋል።

<u>ዓምድ 5 - የመስፈሪያ ኮድ</u>፣ ይህ ኮድ በሚሰጠው የኮድ ዝርዝር መሠረት በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ምርቶች ለእያንዳንዳቸው በዓምድ 3 በተሞላው የሜትሪክ መለኪያ መሠረት በኤዲተሩ ኮድ የሚደረግ ይሆናል። በተጨማሪም በምርት ኮድ መመሪያ ላይ እያንዳንዱ የምርት ዓይነት በምን ዓይነት መለኪያ መሰጠት እንዳለበት ተገልጿል።

<u>ዓምድ 6 - የአንዱ ዕቃ መካከለኛ የሽያጭ ዋጋ</u>፣ በዚህ ዓምድ ሥር ለእያንዳንዱ በዓምድ 2 ለተዘረዘረው የምርት ዓይነት በዓምድ 3 በቀረበው መስፈሪያ መሠረት

አማካይ ዋጋ በብርና በሣንቲም የሚመዘገብበት ስለሆነ በዚሁ መሠረት መፈጸሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የአንዱ ዕቃ መካከለኛ ዋጋ ሊታሰብ ከሚችለው በላይ ወይም በታች አለመሆኑን ማየት ተገቢ ነው።

ዓምድ 7 - የምርት መጠን፣ በዓምድ 2 ለተዘተዘሩት ምርቶች በዓምድ 3 ላይ በተሞላው የሜትሪክ መለኪያ መሠረት በ1996 ዓ.ም የተመረተው መጠን የሚመዘገብበት ስለሆነ በዚሁ ሃሣብ መሠረት መፈጸሙ መረጋገጥ ይኖርበታል።

ዓምድ 8 - ዓመታዊ ምርት በሽያጭ ዋጋ፣ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ምርቶች ለእያንዳንዳቸው በዓምድ 7 ላይ የተመዘገበው ዓመታዊ የምርት መጠን በዓመቱ በነበረው አማካይ የሽያጭ ዋጋ መሠረት ሊያወጣ የሚችለው ዋጋ በብር መስፈሩን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ይህንንም ለማመሳከር የአንዱ ዕቃ መካከለኛ የሽያጭ ዋጋ (በዓምድ 6 የተመዘገበው) ሲባዛ በዓመታዊ የምርት መጠን (በዓምድ 7 የተመዘገበው) ዓመታዊ ምርት (ምርቱ ፋብሪካውን ለቆ ሲወጣ) (ዓምድ 8) ጋር ተቀራራቢ ቁጥር መስጠት ይኖርበታል። ሆኖም በመጀመሪያ በዓምድ 6 የተሞላው ቁጥር ከሚገመተው በላይ ወይም በታች አለመሆኑን ማየት ተገቢ ነው። በዚህ ክፍል የሚሞላው ጠቅላላ የምርትና የሽያጭ ዋጋን እንዲሁም በሽያጭ ላይ የሚከፈሉ ልዩ ልዩ ታክሶችን መጨመር ይኖርበታል። በትርፍና ኪሣራ መግለጫዎች ላይ ብዙ ጊዜ የሚሞላው የሽያጭ ታክሶችን ሳይጨምር ስለሚሆን በመጠይቁ ላይ የሚሞላው ጠቅላላ ሽያጭ (Gross Sales) የበለጠ መሆን ይገባዋል።

ዓምድ 9 - ጠቅላላ የምርት ሽያጭ ብዛት፣ ከክምችትና ከዓመታዊ ምርት በዓመቱ የተሸጠው ጠቅላላ መጠን በዓምድ 3 በቀረበው መስፈሪያ መሠረት የሚሞላበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከዓምድ 7-10 የተሞላውን ከጥሬ ዕቃ ፍጆታ ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ዕቃ ፍጆታ ከተመረተው ጋር ያልተገናዘበ ሊያጋጥም ይችላል። ለምሣሌ:- አንድ ኩንታል የቅባት እህል የተጠቀመ ፋብሪካ የዘይት ምርቱ ከ2 እጅ በታች እንደሚሆን ይጠበቃል። አንድ የዱቄት ፋብሪካ ያመረተው የዱቄት መጠን ከተጠቀመው የስንዴ መጠን ከ65-80% ሊሆን ይገበዋል። በተለይ የተጋነኑ ልዩነቶችን እንደገና መመርመር ያስፈልጋል።

ዓምድ 10 - ጠቅላላ ዓመታዊ የምርት ሽያጭ፣ ከክምችትና ከዓመታዊ ምርት በዓመቱ የተሸጠው ጠቅላላ ዋጋ መስፈር ይኖርበታል። ዓምድ 8 እና ዓምድ 10 እኩል

የሚሆኑት በዓመቱ መጀመሪያ ላይም ሆነ መጫረሻ ላይ የነበረው የክምችት ዋጋ እኩል ሲሆን ወይም በሁለቱም ወቅት ምንም ስቶክ በማይኖርበት ወቅት ብቻ ነው፡፡ ካለበለዚያ ግን የክምችት ልዩነት ከዜሮ በታች (ነጋቲቭ) ከሆነ ዓመታዊ የምርት ዋጋ ከዓመታዊ የሽያጭ ዋጋ ማነስ ይኖርበታል፡፡ በተቃራኒው የክምችት ልዩነት ከዜሮ በላይ (ፖዘቲቭ) ከሆነ ዓመታዊ የምርት ዋጋ ከዓመታዊ የሽያጭ ዋጋ መብለጡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የአንዱን ዕቃ የሽያጭ ዋጋ በማስላት ከሚገመተው በታች ወይም በላይ አለመሆኑን ማየት ተገቢ ነው፡፡

<u>ዓምድ 11 - ከጠቅላላ ሽያጭ ወደ ውጪ የተላከ፣</u> በዚህ ዓምድ ላይ የሚሞላው የሽያጭ መጠን በዓምድ 9 ላይ ከተሞላው ጋር እኩል ሊሆን ወይም ሊያንስ ይችላል እንጂ ሊበልጥ ስለማይችል ይህንኑ ማርጋገጥ ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻም ዓምድ 8፣ 10 እና 11 የተሞላውን ቁጥር ቁልቁል በመደመር ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**4.2 <u>በ1996 ዓ.ም ፋብሪካው ከምርት ሽያጭ ሌላ ያገኘው ልዩ ልዩ ተጨማሪ ገቢዎች (በብር)፣</u>**

ቀደም ሲል በተገጸው መሠረት በዚህ ክፍል ዓምድ 4 ላይ ገቢ ካለ በክፍል 6.2 ዓምድ 12 ላይ ወጪ መኖር ይገባዋል፡፡ አንዳንድ ፋብሪካዎች በተለይ ልብስ ሰፊዎች ጥሬ ዕቃው ከደንበኛው ሆኖ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለሚሠሩ ገቢው የሚመዘገበው በ4.1 ላይ ሳይሆን በ4.2 ዓምድ 2 ውስጥ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የጥሬ ዕቃ ወጪ ለዚህ ፋብሪካ ምንም ዓይነት ሥራ በራሱ ጥሬ ዕቃ ካልሠራ በ6.1 ላይ ስለማይመዘገብ ይህንኑ ማርጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም ፋብሪካው የማይመለከታቸው ዓምዶች ሠረዝ ከተደረጉ በኋላ ከዓምድ 2-10 ሲደመር ዓምድ 11 መስጠቱን ማመሳከር ይኖርብናል፡፡

## <u>ክፍል 5 - በፋብሪካው በ1996 ዓ.ም መጀመሪያና መጨረሻ የነበረው የምርቶችና ዕቃዎች ክምችት ዋጋ</u>

በዚህ ሥር ዓምድ 4 ሲቀነስ ዓምድ 3 ዓምድ 5 መስጠቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡ በተጨማሪም በንዑስ ክፍል 4.1 ዓምድ 10 ላይ በቀረበው ማብራሪያ መሠረት የዓመታዊ ምርትና የዓመታዊ ሽያጭ ዋጋን በዚህ ክፍል በተራ ቁጥር 1 እና 2

ከቀረበው የስቶክ ዋጋ ጋር ማነፃፀር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ክፍል የተሞላው የክምችት ዋጋ ዝርዝር በሂሣብ ሪፖርት ላይ ከተመለከተው ጋር እኩል ወይም ተቀራራቢ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል 6 - በ1996 ዓ.ም ፋብሪካው ለተጠቀመባቸው ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች ወጪና ሌሎች ወጪዎች፣</u>

**6.1 *<u>ፋብሪካው በ1996 ዓ.ም የተጠቀመባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎችና ማሸጊያዎች፣ ወዘተ...መጠንና ዋጋ፣</u>***

***<u>ዓምድ 3 መስፈሪያ</u>*፣ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ጥሬ ዕቃዎች በዚህ ዓምድ መስፈሪያቸው በሜትሪክ መለኪያ መሰጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከሜትሪክ መለኪያ ውጭ ለተሞላላቸው ከፋብሪካው (ከሚመለከተው ክፍል) ጋር በመነጋገር ማስተካከያ መደረግ ይኖርበታል፡፡**

***<u>ዓምድ 5 የመስፈሪያ ኮድ</u>*፣ ይህ ኮድ በሚሰጠው የኮድ ዝርዝር መሠረት በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ጥሬ ዕቃዎች ለእያንዳንዳቸው በዓምድ 3 በተሞላው የሜትሪክ መለኪያ መሠረት በኤዲተሩ የሚሞላ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በጥሬ ዕቃ ኮድ መመሪያ (ዝርዝር) ላይ እያንዳንዱ የጥሬ ዕቃ ዕይነት በምን ዓይነት መለኪያ መለካት እንዳለበት ተገልጿል፡፡**

***<u>ዓምድ 4 - የጥሬ ዕቃ ኮድ</u>*፣ ይህ ኮድ የሚሞላው በጥሬ ዕቃ ኮድ ዝርዝር ላይ ኮድ ለተሰጣቸው ጥሬ ዕቃዎች ብቻ ነው፡፡ ለሌሎች ጥሬ ዕቃዎች ዓምዱ በሠረዝ ይታለፋል፡፡**

***<u>ዓምድ 6፣ 8 እና 10 - የጥሬ ዕቃዎች ብዛት (መጠን)</u>*፣ በዓምድ 6 እና 8 በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ጥሬ ዕቃዎች በዓምድ 3 በተሰጠው መስፈሪያ መሠረት ፋብሪካው በ1996 ዓ.ም. ከሀገር ውስጥና ከውጭ የተጠቀመባቸውን ጥሬ ዕቃዎች መጠን በመለያየት የምንመዘግብባቸው ዓምዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ዓምድ 6 + ዓምድ 8 በዓምድ 10 የተመዘገበውን ጠቅላላ ብዛት መስጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡**

***<u>ዓምድ 7፣ 9 እና 11 - የጥሬ ዕቃዎች፣ ወዘተ... ዋጋ</u>*፣ ከላይ ለመጠን አመዘጋገብ በተጠቀሰው መንገድ ዓምድ 7 እና 11 ላይ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር**

ፋብሪካው በ1996 ለተጠቀመባቸው ጥሬ ዕቃዎች የከፈለውን ዋጋ መመዝገቡንና የሁለቱ ዓምዶች ድምር ዓምድ 11ን መስጠቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: በተጫማሪም የአንዱን ዕቃ ዋጋ በማስላት ከሚገመተው በላይ ወይም በታች አለመሆኑን ማየት ተገቢ ነው:: አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ዕቃ ፍጆታ ከምርት ጋር ሳይገናዘብ ሊሞላ ስለሚችል ከምርት ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል::

በመጨረሻም ዓምድ 11 ቁልቁል ሲደመር በተራ ቁጥር 10 ድምር በሚለው አቅጣጫ ዓምድ 7 + ዓምድ 9 ጋር እኩል መሆኑን በማመሳከር ስህተት ካለ ከተስተካከለ በኋላ በሂሣብ ሪፖርት ላይ ካለው ቀጥተኛ የሆነ የጥሬ ዕቃ ወጪ (Direct raw material) እና ቀጥተኛ ያልሆነ የጥሬ ዕቃ ወጪ (Indirect raw material) ጋር እኩል ወይም ተቀራራቢ መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው::

**6.2 በ1996 ዓ.ም ሌሎች ለማምረት ሥራው በቀጥታ ለዋሉ ወጪዎች የተከፈለ (በብር)፣**

በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር ከቀረቡት ዓምዶች መካከል በተለይ ዓምድ 8 የኤሌክትሪክ ወጪ ለሁሉም ፋብሪካዎች መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: ምክንያቱም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ትርጉም ላይ እንደተገለጸው እነዚህ ፋብሪካዎች በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ከጄነሬተርም ሆነ ከመብራት ኃይል በሚገኝ ኤሌክትሪክ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ነው:: በተጨማሪም በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው በጥያቄ 4.2 ዓምድ 4 በተገዙበት ሁኔታ ተመልሰው ከተሸጡ ዕቃዎች የተገኘ ገቢ ካለ በዚህ ጥያቄ ዓምድ 12 በተገዙበት ሁኔታ ለተሸጡ ዕቃዎች የተደረገ ወጪ መኖር ይገባዋል:: በዚሁ ክፍል ዓምድ 6 ላይ የሚሞላው የነዳጅና የቅባት ወጪዎች ለፋብሪካው ሞተሮች ለኃይል ማመንጫነትና ለቅባት የዋለውን እንጂ ለትራንስፖርት የዋለውን ነዳጅና ለኤሌክትሪክ ማመንጨት የዋለውን ነዳጅ ስለማይጨምር የተጋነነ ቁጥር ከተገኘ (በተለይ ከሲሚንቶ፣ ከብርጭቆና ከሸክላ ፋብሪካዎች ውጪ ላሉት) የትራንስፖርት ሊሆን ስለሚችል እንደገና ተጠይቆ የትራንስፖርት ከሆነ በዚሁ ንዑስ ክፍል 6.3 ዓምድ 6 ውስጥ መግባት ይኖርበታል:: ኤዲተሩ እነዚህን ከመረመረ በኋላ ጥያቄው የማይመለከታቸውን ዓምዶች ሠረዝ በማድረግ ከዓምድ 6-13 (ዓምድ 7ን ሳይጨምር) ሲደመሩ ዓምድ -14 መስጠታቸውን ማመሳከር ያስፈልገዋል::

**6.3 <u>በ1996 ዓም ሌሎች ከምርት ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ለሌላቸው የተደረጉ ውጪዎች (በብር)፣</u>**

**በዚህ ክፍል በዓምድ 11 ላይ የሚሞላው የኢንሹራንስ ክፍያ ለቋሚ ንብረት ብቻ የተከፈለ እንጂ የሕይወት ኢንሹራንስን እንደማያካትት ማረጋገጥ ይኖርብናል:: በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ፋብሪካው በዓመቱ ያላወጣቸው የወጪ ዓይነቶች ሠረዝ ከተደረጉ በኋላ ከዓምድ 2-13 ሲደመሩ ዓምድ 14 መስጠታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚሁ ክፍል ዓምድ 13 ሌሎች ወጪዎች የተሞላው ከጠቅላላ ወጪው ጋር ሲታይ የተጋነነ ከሆነ ዝርዝሩን ጠይቀን ማስተካከል ይኖርብናል::**

**6.4 <u>በ1996 ዓ.ም የተከፈሉ ልዩ ልዩ ታክሶች፣</u>**

**<u>ዓምድ 2 - ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተከፈለ</u> በአብዛኛው ዓመታዊ የሽያጭ መጠናቸው 500,000 ብር እና ከዚያ በላይ የሆኑ ፋብሪካዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ መሆናቸው ይታወቃል:: በመሆኑም በዓምድ ሁለት መሞላት ያለበት በክፍል 4.1 ዓምድ 10 ጠቅላላ የምርት ሽያጫቸው 500,000 ብር እና ከዚያ በላይ ላስሞሉ ድርጅቶች መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል:: ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የሽያጭ መጠናቸው 500,000 ብር በታች የሆኑ ፋብሪካዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፍሉ እንደሚችሉ ማስተዋል ያስፈልጋል::**

**<u>ዓምድ 3 - በምርትና በምርት ሽያጭ ላይ የተከፈሉ ልዩ ልዩ ታክሶች</u>፣ ብዙዎቹ ፋብሪካዎች (ከምግብ ፋብሪካዎች በስተቀር) የሚከፍሉት ከ7-12 በመቶ የሽያጭ ወይም የምርት ዋጋቸውን አካባቢ ሲሆን የመጠጥ ፋብሪካዎች ግን ኢክሳይዝ ታክስ ስለሚከፍሉ ከዚህም በላይ በጣም ከፍ ያለ ፐርሰንት ሊከፍሉ እንደሚችሉ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የዚህ ንዑስ ክፍል ጥያቄ የማረም ሥራ መከናወን ይኖርበታል:: ስለሆነም ይህ ንዑስ ክፍል ላይሞላ የሚችለው ምን አልባት ለምግብ ፋብሪካዎች እንጂ ለሌሎች መሞላት ይኖርበታል::**

**<u>ዓምድ 4 - ለኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ</u> የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈሉት የተወሰነ የፋብሪካ ዓይነቶች እንደ ኬሚካል የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ ይህም የብር መጠን ከሽያጭ ታክስ ጋር ተደባልቆ አለመግባቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::**

ዓምድ 5 - በትርፍ ላይ የተከፈለ ግብር፣ የሂሣብ መዝገባቸው (ትርፍና ኪሣራ መግለጫቸው) በአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ተቀባይነት ያለው ፋብሪካዎች ብዙውን ጊዜ የሚከፍሉት የትርፋቸውን 35% አካባቢ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ንዑስ ክፍል ጥያቄ ላይ መሞላት ያለበት የዓመቱ ትርፍ ግብር መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም የሂሣብ መዝገብ ላላቸው ብቻ የጠቅላላ ወጪ ድምርና የጠቅላላ ገቢ ድምር በመጠይቁ ላይ ከተሞላው ጋር እኩል ወይም በጣም ተቀራራቢ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም በትርፍና ኪሣራ መግለጫ ላይ የሚገኘው ትርፍ (ኪሣራ) በመጠይቁ ላይ ከተሞላው ጠቅላላ ገቢ ሲቀነስ ጠቅላላ ወጪ (ክምችትን ግምት ውስጥ በማስገባት) ጋር እኩል ወይም በጣም ተቀራራቢ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## ክፍል 7 - በ1996 ዓ.ም የፋብሪካው ቋሚ ንብረትና መዋዕለ ዋጋ (በብር)፣

7.1 በ1996 ዓ.ም በቋሚ ንብረትና የመዋዕለ ነዋይ መጠን በቋሚ ንብረት ዓይነት

ዓምድ 3 - በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ያለው የዋጋ ግምት፣ የሂሣብ መዝገብ ላላቸው ፋብሪካዎች በዓመቱ መጀመሪያ ያለው ዋጋ ማለት በ1996 ዓ.ም የፋብሪካው የሂሣብ ዘመን መጀመሪያ ላይ ያለው የዋጋ ግምት በዓምድ 2 በተዘረዘሩት የቋሚ ንብረቶች ዝርዝር መሠረት ይሞላል፡፡ የሂሣብ መዝገብ የሌላቸው ሆነው በግምት ሞልተው ከላኩትና በምትኩ የቋሚ ንብረት ዓይነቶችን ዘርዝረው የተገዙበትን/የተሠሩበትን ዋጋና ዓ.ም. በየዓመቱ ለመዋዕለ ንዋይ ወጭ የሆነውን ለገለጹ ፋብሪካዎች በሚሰጠው ስታንዳርድ የአገልግሎት ቅናሽ ስሌትን መሠረት በማድረግ በዓመቱ መጀመሪያ ያለው የዋጋ ግምት በኤዲተሩ ይሠራል፡፡ ዓምድ 6 የዓመቱ የአገልግሎት ቅናሽ እጅግ ቢበዛ ከ20 በመቶ በላይ ከሆነ የተጠራቀመ የአገልግሎት ቅናሽ ሊሆን ስለሚችል እንደገና ፋብሪካውን ወይም የሚመለከተውን ክፍል በማነጋገር ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 7 - በዓመቱ መጨረሻ የተጣራ የንብረት ዋጋ፣ በዓምድ 2 ውስጥ ለተዘረዘሩት የቋሚ ንብረት ዓይነቶች ለእያንዳንዳቸው በ1996 መጨረሻ የነበራቸውን የዋጋ ግምት ትክክለኛነት ለማወቅ (ዓምድ 3 + ዓምድ 4) - (ዓምድ 5 + ዓምድ 6)= ዓምድ 7 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ዓምድ 7 ቁልቁል

ሲደመር በተራ ቁጥር 7 ድምር በሚለው አቅጣጫ (ዓምድ 3 + ዓምድ 4) - (ዓምድ 5 + ዓምድ 6) ጋር እኩል መምጣት ይኖርበታል:: በመጨረሻም የሂሣብ ሪፖርት ላላቸው የዓምድ 3 ድምር፣ የዓምድ 8 ድምር፣ የዓምድ 7 ድምር፣ ከሂሣብ ሪፖርት (NET BOOK VALUE) ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል::

**7.2 በ1996 ዓ.ም ለቋሚ ንብረትና ሥራ ማስኬጃ የተደረገ ወጪ በምንጭ፣**

__ዓምድ 3 -__ በዚህ ዓምድ ፋብሪካው በ1996 ለቋሚ ንብረት ወጪ ካደረገ የገንዘቡ መጠን በተዘረዘሩት የምንጭ ዓይነቶች መሞላቱን ማረጋገጥ ያለብን ሲሆን የዚህ ዓምድ ድምር በክፍል 7.1 ዓምድ 4 ከተጠቀሰው ድምር ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል::

__ዓምድ 4 -__ በዚህም ዓምድ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ወጪ በምንጩ ዓይነት መዘርዘሩንና ድምሩም ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ክፍል 3.1 ዓምድ 16፣ ክፍል 3.2 ዓምድ 6-9፣ ክፍል 6.1 ዓምድ 11 ድምር፣ ክፍል 6.2 ዓምድ 14፣ ክፍል 6.3 ዓምድ 14 ( ዓምድ 9ን ሳይጨምር ) እና ክፍል 6.4 ዓምድ 2-4 ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## __ክፍል 8 -በ1996 ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ የማምረት ችሎታው፣__

**8.1 ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ የማምረት ችሎታው፣**

__ዓምድ 3 - መስፈሪያ፣__ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ፋብሪካው ለሚያመርታቸው ዋና ምርቶች በዚህ ዓምድ መስፈሪያቸው በሜትሪክ መለኪያ መሰጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከሜትሪክ መለኪያ ውጭ ለተሞላላቸው ከፋብሪካው (ከሚመለከተው ክፍል) ጋር በመነጋገር ማስተካከያ መደረግ ይኖርበታል:: በተጨማሪም በምርት ኮድ ዝርዝር ላይ በተሰጠው አማራጭ የመለኪያ ዓይነት ውስጥ መሆኑን ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 5 - የመስፈሪያ ኮድ፣ ይህ ኮድ በሚሰጠው የኮድ ዝርዝር መሠረት በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ምርቶች ለእያንዳንዳቸው በዓምድ 3 በተሞላው የሜትሪክ መለኪያ መሠረት በኤዲተሩ ኮድ የሚደረግ ይሆናል።

ዓምድ 4 - የምርት ኮድ፣ ይህ ኮድ የሚሞላው በሚሰጠው ዝርዝር የምርት ኮድ ላይ ለሚገኙ የምርት ዓይነቶች ብቻ ነው። ለሌሎች በሠረዝ ይታለፋል።

ዓምድ 6-7፣ በዓመት ሊመረት የሚችል መጠንና ዋጋ፣ ለእያንዳንዳቸው በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የምርት ዓይነቶች በነዚህ ዓምዶች የሚሞላው መጠንና ዋጋ በ4.1 ዓምድ 7 እና 8 ከተሞላው መጠንና ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እኩል ሊሆን ወይም ሊበልጥ ይችላል እንጂ ሊያንስ ስለማይችል ይህንኑ ማርጋገጥ ይኖርብናል። በተጨማሪም በዚህ ንዑስ ክፍል የዓምድ 7 ድምርን ትክክለኛነት ከአረጋገጥን በኋላ በንዑስ ክፍል 4.1 የዓምድ 8 ድምር ጋር በተመሳሳይ መንገድ ማነፃፀር ያስፈልጋል።

8.2 በ1996 ዓ.ም. ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ የሚያስፈልገው የጥሬ ዕቃ መጠንና ዋጋ፣

በዚህ ንዑስ ክፍል የተሞላው መጠንና ዋጋ በንዑስ ክፍል 6.1 ከተሞላው መጠንና ዋጋ ሊበልጥ ይችላል እንጂ ሊያንስ ስለማይችል ይህንኑ ማረጋገጥ ይኖርብናል። በተጨማሪም ይህ ዓምድ በንዑስ ክፍል 6.1 ላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት መሞላቱን ማየት ያስፈልጋል።

8.3 የማምረቻ ኢንዱስትሪው በ1996 የምርት ዘመን ያመረተው የምርት መጠን ከማምረት አቅሙ ምን ያህል እንደሆነ በመቶኛ ይገለጽ፣

በዚህ ጥያቄ ሥር ድርጅቱ በ1996 ያመረተውን የምርት መጠን ከማምረት አቅሙ ጋር በማገናዘብ የድርጅቱ ባለቤት ተጠይቆ የሚሞላ በመሆኑ በዚህ መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥና ከ100 በላይ አለመሞላቱን ማረጋገጥም ያስፈልጋል።

**8.4** <u>ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ካልሠራ ያልሠራበት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ምን እንደነበሩ ይገለጽ</u>፣

በዚህ ጥያቄ ሥር ከ1-8 ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ሶስት ኮዶች ብቻ መከበባቸውንና እነዚህ የተከበቡ ኮዶች በኮድ መስጫው ሣጥኖች (ካርድ ኮለሞች) ውስጥ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያለብን ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ግን መልሱ ከሶስት ሊበልጥ ባይችልም ከሶስት ያነሰ መልስ ግን ሊሞላ ስለሚችል ማስተካከሉ በዚሁ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

**8.5** <u>የገበያ ችግር ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው</u>? ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በጥያቄ 8.4 ኮድ 3 ለሞሉ ወይም የገበያ እጦት ብለው ምክንያታቸውን ለገለጹ ፋብሪካዎች ስለሆነ ይህን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጥያቄ ሥር የተከበበው ቁጥርና በካርድ ኮለሙ የተሞላው አንድ ዓይነት መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

**8.6** <u>የሥራ ማስኬጃ እጥረትን ለመቅረፍ ከብድር ተቋማት ብድር ለማግኘት ሞክሮ ነበርን</u>? ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በጥያቄ 8.4 ኮድ 4 ላስሞሉ ፋብሪካዎች ብቻ ስለሆነ ይህንኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪ በዚህ ጥያቄ ሥር የተከበበው ቁጥርና በካርድ ኮለሙ የተሞላው አንድ ዓይነት መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

**8.7** <u>የሥራ ማስኬጃ እጥረቱ ያልተቀረፈበት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው</u>? ይህ ጥያቄ የሚመለከተው ለጥያቄ 8.6 ኮድ አንድ ወይም አዎ ብለው ለመለሱ ፋብሪካዎች ብቻ ስለሆነ ይህንኑ ማረጋገጥ ይኖርብናል በተጨማሪም ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡት መልሶች ከሁለት በላይ ስለማይሆን እነዚህ የተሰጡት መልሶች በካርድ ኮለሙ ከተሞሉት ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**8.8** <u>ፋብሪካው በአሁኑ ወቅት ሥራውን ለማከናወን ያጋጠሙት ሦስት ዋና ዋና ችግሮች ምንድን ናቸው</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር ከ1-11 ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ሦስት ኮዶች ብቻ መከበባቸውንና እነዚህ የተከበቡ ኮዶች በኮድ መስጫው ሳጥኖች ውስጥ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያለብን ሲሆን አንዳንድ ጊዜ መልሱ ከሦስት ሊበልጥ ባይችልም ከሦስት ያነሰ መልስ ግን ሊሞላ ስለሚችል ማስተካከሉ በዚሁ መሠረት መፈፀም ይኖርበታል፡፡

**8.9** ***<u>ፋብሪካው ምርቱን ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ ያጋጠሙት ችግር አለ</u>? ይህ ጥያቄ የሚመለከተው ምርቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ፋብሪካ ብቻ ሲሆን እነዚህ ፋብሪካዎች የተመለሰው መልስ በካርድ ኮለሙ ጋር አንደ ዓይነት መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡***

**8.10** ***<u>ምርትዎን ወደ ውጭ በመላክ ሂደት ያጋጠመዎት ዋና ዋና ችግሮች ምንድን ናቸው</u>? ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በጥያቄ 8.9 ኮድ አንድ ላስሞሉ ብቻ ስለሆነ ይህንን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡***

**8.11** ***<u>ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚጠቀመው ጥሬ ዕቃ የውጭ ሀገር ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው</u>? በዚህ ጥያቄ ሥር ከ1-6 ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ ኮድ ብቻ መከበቡን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በክፍል 6.1 ዓምድ 9 የውጭ ሀገር ምርት ላስሞሉ ድርጅቶች ብቻ ስለሆነ ይህንኑ ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡***